**አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ህይወት ትምህርት ላይ የወላጆች በምርጫ የማስተማር ፎረም - 5ኛ ክፍል**

የተማሪው ስም : ________________________________ስልክ ቁጥር: ___________________
የአስተማሪው ስም: _________________________________ቀን: _______________________

እኔ እዚህ ያለሁት ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ልጄ እንዳይሳተፍ የምፈልግበትን ምርጫ እንዳደርግ ነው። ልጄ እንዳይሳተፍ በማደርግባቸው አላማዎች ላይ፣ ልጄ ያለምንም ተፅእኖ አማራጭ አሳይመንቶች እንደሚሰጡት ተረድቻለሁ። ልጄ አሳይመንት በሚሰራበት እና ለአሳይመንቱ ውጤት በሚሰጥበት ወቅት፣ በትምህርት ቤቱ ህጎች እና ፖሊሲዎች መመራት እንደሚጠበቅበት ተረድቻለሁ።

<u>**አቅጣጫዎች:**</u> እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አላማዎች ላይ ልጅዎ እንዳይሳተፍበት የሚፈልጉትን ነገር ካለ ምልክት ያድርጉበት።

___ **5.1 ተማሪው ስለኦንዶክሪን ስርአት አወቃቀር እና ተግባር ይገልፃል።**
<u>መግለጫ</u>: የኢንዶክሪን ስርአት ዋና ዋና ክፍሎች (ፒቱተሪ እጢ እና አድሬናሊን እጢ ሲሆኑ) እና ክፍሎቻቸው እና ተግባራቸውን እንዲያውቁ ይደረጋል።

___ **5.2 ተማሪው የሰው ከጠቅላላ የሰውነት ክፍል ውስጥ የመራቢያ አካላትን እነማን እንደሆኑ እኒለይ ይደረጋል።**
<u>መግለጫ</u>: በወንዶች የመራቢያ አካላት፡ የወንድ ብልት፣ ቴስቲክልስ፣ ስክሮተም፣ አርቴሪያ እና በሴቶች የመራቢያ አካላት፡ ማህፀን፣ ኦቫሪስ፣ የሴት ብልት እና ፋሎፒያን ትዩብ ላይ ትኩረት ይደረግባቸዋል። እነዚህ የመራቢያ አካላት ከጠቅላላው የሰውነት ክፍል ጋር ጎን ለጎን የሚገለፁ

___ **5.3 ተማሪው ሰዎች እንዴት እንደሚራቡ ያስረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: መመሪያው በውስጡ የሚይዘው ስፐርም እና እንቁላል እንዴት እንደሚገናኙ እና ፅንስ ማህፀን ውስጥ እንዴት እንደሚያድግ ነው። የህፃኑ እድገት በተለያየ ደረጃ በስእል ይታያል። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ፆታዊ ግንኙነት መዘዝ እንዳለው በትኩረት ይታያል። የቅድመ ወሊድ ክትትል አስፈላጊነት እና አደንዛዥ እፆች በእናትየው እና በሚወለደው ልጅ ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ለውይይት የሚቀርቡ ርእሶች ናቸው።

___ **5.4 ተማሪው በጉርምስና ወቅት ስለሚከሰተው አካላዊ ለውጥ እና ግንኙነት ለማድረግ አቅም እንደሚያዳብር ይረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: በጉርምስና ወቅት ስለሚከሰቱ አካላዊ ለውጦች ማጠቃለያ ይሰጣል። ከሚካተቱት ርእሶች ውስጥ የወንድ ብልት መቆም እና በማታ የሀር ፍሬን ስለመልቀቅ፣ ስለወር አበባ፣ በጉርምስና ወቅት ስለሚከሰቱ የስሜት አለመረጋጋቶች ልክ እንደ ስሜት መለዋወጥ፣ ለአንድ ሰው የግብረ ስጋ ግንኙነት አዎንታዊ ፍላጎት ማሳየት እና በጉልምስና ወቅት የሚከሰቱ ለውጦች ምክንያት የአንድ ሰው ልጅ የመውለድ አቅም ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው።

___ **5.5 ተማሪው የተመጣጠነ ምግብ ለእሱ ወይም ለእሷ እና ለእርጉስ ሴት አስፈላጊ እንደሆነ እና ፅንሱ በማህፀን ውስጥ ሲያድግ አደንዛጭ እፆችን መጠቀም አደጋ እንደሚያስከትል ይገነዘባል።**
<u>መግለጫ</u>: የዚህ ትምህርት አላማ ከአምስተኛ ክፍል የጤና ስርአተ-ትምህርት ውስጥ ከሚገኘው የምግብ ትምህርት ጋር የተገናኘ ነው።

___ **5.6 ተማሪው ከጋብቻ በፊት የግብ-ስጋ ግንኙነት መደረግ የሌለበትን ምክንያቶች ይለያል።**
<u>መግለጫ</u>: ከጋብቻ በፊት የሚደረጉ የግብረ-ስጋ ግንኙነቶች የሚኖራቸው ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ እና አካላዊ ጉዳቶች እና በአካል እና በስሜት እስክንበስል ድረስ የግብረ-ስጋ ግንኙነትን የማዘግየት ያለው ጥቅምም ለውይይት የሚቀርብ ይሆናል።በአስራዎቹ እድሜ ውስጥ የሚደረግ የግብረ-ስጋ ግንኙነት፤ ልጅነት እርግዝናን፣ የፅንስ ሞትን እና በፆታዎ ግንኙነት ወቅት ለሚተላለፍ ኢንፌክሽን እንደሚያጋልጥ እና በስም ላይ፣ በራስ መተማመን እና በአእምሮ ጤንነት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

___ **5.7 ተማሪው የግል ንፅህናን መጠበቅ በራስ አመለካከት ላይ ስለሚኖረው ተፅእኖ ያስረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: ውይይቱ ትኩረት የሚያደርገው በጉልምስና ወቅት በሚከሰቱ ለውጦች ምክንያት ለንፅህና ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ እና ለራስ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረን እና በእኩዮቻችን ዘንድ ተቀባይነት እንድናገኝ እንደሚረዳን የሚያስረዳ ነው። ከንፅህና ጋር በተያያዘም በወር አበባ ወቅት ተገቢውን የንፅህና መጠበቂያ መሳሪያዎችን መጠቀምንም ያካትታል።

___ **5.8 ተማሪው በቡድን ስራ ወቅት አስተዋፅኦ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ይገነዘባል።**
<u>መግለጫ</u>: አስተማሪው እያንዳንዱ ግለሰብ በግል ደረጃ ሀላፊነትን ለመቀበል የሚያሳየው ፈቃደኝነት ለቡድኑ ስኬትም ወይም ውድቀት ያላውን አስተዋፅ  እና መሪ የመሆን እድልም እንዴት እንደሚገኝ ትኩረት ሰጥቶ ያስረዳል።

___ **5.9 ተማሪው የቤተሰብ አባላትን ሚና፣ ግዴታዎችን እና ሀላፊነቶችን ምን እንደሆነ ግንዛቤን ያዳብራል።**
<u>መግለጫ</u>: ተማሪው ይህንን ማሳካት የሚችለው፤ የቤተሰቡ አባላት ያላቸውን ባህላዊ እና የለውጥ ሚናዎችን፣ ግዴታዎችን እና ሃለፊነቶችን በመግለፅ፣ ለሚለዋወጡ ሚናዎች በህይወት ዘመኑ ለሚጠበቅበት ግዴታዎች በመዘጋጀት እና የቤተሰብ አባል በመሆን ምክንያት ስለሚኖረው የስሜት መግበባት በመግለፅ ነው። ባህላዊ ያልሆኑ የወንድ እና የሴት ሚናዎች እና የእድሜ ልክ ግቦች ምን እንደሆኑ ይቀርባሉ።

___ **5.10 ተማሪው ከፆታዊ ግንኙነት ጋር በተያያ በሚዲያ የሚተላለፉ መእልክቶችን ይገመግማል።**
<u>መግለጫ</u>: የታተሙ መፅሀፍት፣ ማስታወቂያዎች፣ ቴሌቭዥን፣ አልባሳት፣ ኢንተርኔት፣ ፊልሞች እና ሙዚቃ ከፆታዊ ብዝበዛ እና ከወሲባዊ ብዝበዛ ጋር ያላቸውን ግነኙነት እና ኤሌክትሮኒክሶችን በመጠቀም ወሲባዊ ብዝበዛ ሊደርስም እንደሚችል ይወያያሉ።  ተማሪዎችን ስልክን እና ማህበራዊ ድህ-ገፆችን በተገቢው መንገድ መጠቀም እንዳለባቸው ይረዳሉ። ተማሪዎች ማህበራዊ ድህረ-ገፆች ከወሲብ ጋር በተያያዘ በአእምሮ ላይ ስለማደርሱት የጤና ጉዳት ይረዳሉ።

___ **5.11 ተማሪው ለእሱ/ሷ መጥፎ ለመሰለው ማንኛውም ነገር ወይም ማህበራዊ ባህሪ ‘አይሆንም’  የማለት ልምድ ያዳብራል።**
<u>መግለጫ</u>: ውይይቱ ትኩረት የሚደርገው መጥፎ ባህሪ፣ ማጨስ፣ አልኮል ወይም አደንዛዥ እፅ መጠቀም፣ መስረቅ፣ መጥፎ ስራ መስራት፣ ሁከት መፍጠር እና ያለእድሜ ወይም ያልተፈለገ የግብራ ስጋ ግንኙነትን ከማድረግ ይልቅ ያሉ አማራጭ ሁኔታዎች ላይ ነው።

___ **5.12 ተማሪው ለማስፈራሪያዎች ወይም ለማይመቹ ሁኔታዎች እንዴት መመለስ እንዳለበት ይገነዘባል።**
<u>መግለጫ</u>: እነዚህ ሁኔታውች የሚያካትቱት፡ ብቻ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ ለማይታወቅ ሰው በር መክፈት፣ ወሲባዊ ብዝበዛ ወይም በዘመድ መደፈር፣ በገንዘብ ተፅእኖ የተነሳ ሰውነታቸውን እንዲሸጡ ተፅእኖ ላይ

መውደቅ፣ አላስፈላጊ ነገሮችን በስልክ ወም በፅሁፍ መልእክት መቀበል፣ በገበያ አዳራሾች ውስጥ ለአደጋ መጋለጥ የሚጠቀሱት ናቸው። ራስን መከላከያ መንገዶች እና እንደዚህ አይነት ነገሮች ሲገጥሙ አውቆ ሪፓርት ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ነገሮች ናቸው። ይህ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ቢሆንም አንኳን አብዛኞቹ በህይወታችን የሚገጥሙን ሁኔታዎች ለህይወት አስጊ የሚባሉ አይደሉም።

___ **5.13 ተማሪው መአደንዛዥ እፆችን መጠቀም እና ሰውነትን ላይ ያለአግባብ መጠቀም ያላቸውን ጉዳትይገልፃል።**

<u>መግለጫ</u>: አልኮል፣ አደንዛዥ እፆች እና ሲጋራ በሰውነት ላይ ስላለው መጥፎ ጉዳት ትኩረት ይደረግበታል። . ይህ መረጃ በጉርምስና ወቅት የሚያጋጥሙ አካላዊ እና አእምሮአዊ እድገቶች ጋር የተያያዘ ሲሆን ወሲባዊ እድገት፣ የፅንስ እድገት እና ማንኛውም አይነት በቤተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ችግሮን ያጠቃልላል።

___ **5.14 ተማሪው በግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ ኢንፌክሽን እንዳለ እንዲያውቅ ይደረጋል።**

<u>መግለጫ</u>: ከግብረ-ስጋ ግንኙነት ጋር የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች እንዳሉ በእውነት ላይ ተመረኮዘ መረጃ በመስጠት ይህም ሂውማን ኢሚኒዮ-ዴፊሸንሲ ቫይረስ (HIV)/አኳየርድ ኢሚኒዮ ሲንድረም(AIDS) የሚባሉ እንዳሉ እንዲያውቁ ይደረጋል።ሌሎች የሚጠቀሱ በሽታዎችም ይኖራሉ ግን ክላይሜደን፣ ጄኒታል ኸርፐስ፣ ጎኖሪያ፣ ሂውማን ፓፒሎማ ቫይረስ(HPV) እና ቂጥኝ ብቻ ላይ የተወሰኑ

**ትምህርት ቤታችሁ በወሰነው ቀን መሰረት ይህንን ቅፅ በመሙላት ለርእሰ-መምህሩ እባክዎን ያስረክቡ**

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ: ________________________________________ ቀን: __________